ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ራዲዮ
በሚያዚያ 3 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## "ግመሉ ሲወድቅ ካራዎቹ ይበረክታሉ "

**የዐረቦች ምሣሌ**

ረሀብ ያጠወለገው የበረሃ ነጋዴ ፤ ግመሉ እንዲወድቅለት ይጸልያል። ጸሎቱ ደርሶ ግመሉ ከወደቀለት፤ ሲያሰፈስፍ የቆየው ሁሉ ፤ካራዉን እየሞሸለቀ ግመሉን ለመቀራመት ይሻማል። በየስልቻው ተደበቆ የነበረው ካራ ሁሉ በሚያስደነግጥ ፍጥነትና ስግብግብነት፤ ጊዜ በጣለው ግመል ላይ ይረባረባል። ስጋውን ለመቀራመት ሁሉም ካራ ይራኮታል። በፊት ቀድሞ በመድረስ ፤ ሥጋውን የተቀራመተው በልቶ ሲጨርስ፤ ዘግይቶ የደረሰው ዳተኛ ደግሞ ፤ ፍርፋሬ ሳያገኝ ይቀርና በፈርሱ ላይ ያጓጉራል። የግመሉ መውደቅ ውጤት በሁለት ከስተቶች ይገባደዳል። 1ኛ. የግመሉን ሥጋ የበላው፤ ጊዚያዊ ዕርካትን ያገኛል። 2ኛ. ሥጋውን ለመካፈል ያልቀናው ደግሞ፤ በፈርሱ ላይ እያጓጎረ ይኖራል ። በልቶ የረካውና ሳይበላ ቀርቶ በፈርሱ ላይ የሚያጓጉረው ድምር ውጤት ግን ፤ ዞሮ ዞሮ አንድ ብቻ ነው ። ግመሉን ከምደረ-ገፅ ማጥፋት !

በተቀራማቾቹ ካራ ስለት ከምድረ-ገፅ የጠፋው ግመል ታሪክ ፤ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ነባራዊ ገጽታ ገለጭ ነው ቢባል ፤ እንደ ሟርት አይቆጠርም። ሀገሪቱን ለመቀራመት ያሰፈሰፉት ፀረ-አንድነት ኃይላት፤ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን አጣብቂኝ ሁኔታ፤ ወደሚመኙት ኣላማቸው ስኬት ለመለወጥ በመጓጓት ላይ መሆናቸውን በተግባር እየገለፁት ይገኛሉ። ምን ጊዜም ቢሆን ያንን ስኬት ለማየት ካሁኑ የተሻለ አጋጣሚ እንደማያገኙ አውቀውታል። " ብረቱ ሲግል ቀጥቅጠው ! " እንደሚባለው ሁሉ ፤ "ኢትዮጵያ ስትዳከም አፈራርሳት ! " " ዜጎቿ እርስ በርሳቸው ሲፋጁ፤ በታትናት ! "፤ የሚለውን የቆየ መፈክር በተግባር ለማየት የሚፈልጉ ፅንፈኞች ፤ የዛሬውን ሁኔታ፤ ላሜ ወልደች ብለውታል። ለዐመታት ሲደክሙበት የቆዩትን ምኞት ዕውን ለማድረግ ከአሁኑ የተሻለ ዕድል እንደማያገኙ በሚገባ ተርድተውታል። አጋጣሚው ሁሉ ተመቻችቶላቸዋል ። " ሲሾም ያልበላ፤ ሲሻር ይቆጨዋል " ነውና፤

ወቅታዊው የኢትዮጵያ፤ ሁኔታ የሰገኘላቸውን መልካም ዕድል ተጠቅመው ፤ ዐላማቸውን ለማሳካት በርብርቦሽ ላይ ናቸው።

ጽንፈኛ ብሔረተኞች በሁለንተናዊ ረገድ ፤ ተደራጅተዋል ። በተለያየ ረድፍ ተባስበስዋል። በልዩ ልዩ የትግል ስልት ታጥቀዋል ። ኅብረተሰባቸውን ፤ እነርሱ በሚፈልጉት አቅጣጫ እንዲያተኩር አድርገውታል ። የኃይል ሚዛኑ ወደ እነርሱ ጎራ እንዲያደላላቸው ፤ ሌት -ተቀን በትጋት ይሰራሉ ። የአንድነት ኃይሉን ጎራ ለማዘናጋት በትጥቅ -አስፈች ተውኔት ለማማለል ይጥራሉ። ትላንትና " ወራሪዋ አቢስንያ " እየሉ ሲረግሚት የነበርቸውን ምድር፤ ዛሬ፤ "ኢትዮጵያ ወይ ሞት!" በማለታቸው፤ የሁሉንም ዜጋ ቀልብ ለመሳብ የቻሉ መስሏቸዋል ። በዚኽ ዕሳቤ፤ የዜጎችን ቀልብ መሳብ ፤ ያስደስታል እንጅ አያስከፋም። ያም ሆኖ ግን፤ ነባቢትን ወደ ተጨባጭ ድርጊት መለወጥ ፤ ያስተማምናል ! ያቀራርባል ! ያስተባብራል ! እያዋሃደ የህገን መሠረት ያጠናክራል። የዜግነት ፖለቲካ ለዚኽ ሂደት ዐብነት ሆኖ ያገለግላል። ጽንፈኞች ፤ ከስሜታዊ አባዜ ወደ ምክንያታዊ ባኅርይ እንዲለወጡ ይጠበቅባቸዋል። የጋራ ሀገርን በጋራ እየዳኑ መጠቀም ለሁሉም ዜጋ ይጠቅማል። የማማለል ፖለቲካ ግን፤ ቢከፍቱት ተልባ ነው ። ለማንም አይጠቅምም። ከማስተዛዘብ በቅር፤ መተማመንን አያመጣም።

" ኢትዮጵያ ትቅደም ! " በሚል የማማለያ ቋንቋ በመጠቀም ሥልጣን እንደያዙት የደርግ መኮንኖች ሁሉ፤ እነኝኽም ዛሬ ፤ በተመሳሳይ ቋንቋ የማዘናጊያ አፍዝዝ-አደንዝዝ ምትሃት በማርከፍከፍ ላይ ይገኛሉ ። ይኽ ምትሃት ደግሞ፤ የሀገሩ የኢትዮጵያ ጉዳይ ፤ በአጥንቱና በደሙ ገብቶ የሚያንሰፈስፈውን፤ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፤ በቀቢፀ-ተስፋ እንዲዘናጋ ለማድረግ፤ ጊዜያዊ አቅም አግኝቷል ። ላለፈው 27 ዐመታት ከነበረው የጨለማ ጊዜ፤ ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል መከሰቱን በመገንዝብና ፤ የለውጡን ሁኔታ በአስተዉሎ ዕሳቤ እየተመለከተው መሆኑን ተረድቶ፤ በትዕግስት፤ እየተጠባበቀ ያለውን **"ኢትዮጵያ ሀገሬ"** የሚለውን ዜጋ ፤ በማዘናጋት፤ የራሳቸውን ዐላማ ለማራመድ ተመችቷቸዋል። " ዶሮን ሲያታልሏልት፤ በመጫኛ ጣሏት " የሚለውን ብሂል የሚታዘብ ኅብረተሰብ ፤በማር ቅብ የቀረበለትን መርዝ ለይቶ የማወቅ ችሎታ አለው።

አነሰም- በዛ፤ ለዘውጋዊ ፖለቲካ መመቻቸት፤ የአንበሳውን ሚና የተጫወተው ወያኔ መሆኑ ባያጠራጥርም፤ አክራሪ ብሄረተኞች ግን ሁኔታውን በማጦዝ የሀገሪቱን ፖለቲካዊ መልከዐ- ምድር ፤ ወደራሳቸው ፖለቲካ አግማስ ለመለወጥ በጥድፊያ ለይ ናቸው። ፖለቲካዊ መልከዐ- ምድሩ ብቻ ሳይሆን ፤ ቶፖ-ግራፊውም ጭምር እንደ ቆማርተኞች ካርታ የተበወዘ/ የተመሰቃቀለ በመሆኑ፤ የትኛው ዜጋ

( ሀገረኛ) የት ቦታ መኖር እንዳለበት፤ እርሱ ራሱ ሊወስን ከማይችልበት ጊዜ ተደርሷል። ኢትዮጵያዊውን ዜጋ፤ እንደ ከብት ግጦሽ፤ በክልልና በጎጥ ተሸብቦ እንዲኖር ማድረግ የዜግነት መብቱን ብቻ ሳይሆን ፤ ሰብዓዊ ክብሩንና ልዕልናውንም ጭምር መገፈፍ እንደሆነ ዘውጋዊ ፖለቲካ የሚያራምዱ ሁሉ ሊገነዝቡት አልቻሉም። ወደ የክልልህ ሂድ እያሉ፤ ተወልዶ - ካደገበት፤ ልጅ ወልዶ-ከብዶ መላ ሕይወቱን ካሳለፈበት አካባቢ ማፈናቀል፤ከህግም ሆነ፤ ከሰብዓዊ ሚዛን አኳያ ተቀባይነት አይኖረውም። እጅግ የሚያስተዛዝበው፤ ይህንን በዜጎች ላይ የሚፈፀመውን ሀገራዊ ወንጀል ዛሬ በሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎች አለማስቆማቸው ነው። ዜጎችን የማፈናቀል ደርጊት ከበድ መሆኑን ፤ የወንጀሉ ፈፃሚዎች ሊገነዘቡትም የሚችሉ አይደሉም ። ምክንያቱም፤ የዘረኛ ሥርዓት ጠንሳሾቹና ቀዳሾቹ ወያኔዎቹ ሰለነበሩ፤ እነርሱ ባርከው- ቀድሰው - ጠምቀው- አሰልጥነው ስለአስማሯቸው ያንኑ ለመተርጎም በቅተዋል።

ለዚኽ ሁሉ ምስቅልቅል መሠረት የሆነላቸው፤ ከወያኔ ድርጅታዊ ፕሮግራም የመነጨውን ድርሰት ፤ ወደ ጎሳዊ ህግመንግሥት እንዲሸጋገር ያደረገው ፤ የደበቢት ሣጥናዔል ሠነድ እንደሆነ የአደባባይ ምሥጥር ነው ። ዛሬ በሀገራችን የሚታየው የፖለቲካ፤ የምጣኔ ሀብትና የማኅበራዊ ኑሮ ምስቅልቅል፤ መሠረቱ በዘውግ ላይ የተመሠረተው ይህ ህገመንግሥት ለመሆኑ አያከራክርም ። **የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ምንም ቢሆን ምን፤ አክራሪ ዘውገኞች የለቀለቁትን ሠነድ፤ እንኳንስ የሀገሪቱ ህገ መንግሥት ቀርቶ ፤ እንደ ዕድር መተዳደርያ ወረቀት ቦታ አይሰጠውም ። የዘረኛ ህገመንግሥት፤ የታላቅ ሕዝብ ህገመንግሥት ለመሆን ብቃት የለው።**

በዜግነት እንጅ በዘውግ ላይ የተመሠረተ መንግሥታዊ ሥር ዓት ፤ ለኢትዮጵያ እንደማይበጅ አሁን የሚታየው የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ኸያው ምስክር ሆኗል ። በመሆኑም ዜጎች በህብረት ተጠናክረው ፤ ዘውጋዊ አጋዛዝን በዜጋዊ ሥርዓት የመለወጥ ተግባር ማከናወን አላባቸው። ዜጋዊ አስተዳደርን ለማምጣት ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ ማነኛውንም የትግል ስልትና አካሄድ የመጠቀም መብቱን እያስከበረ ኃይሉን ማጠናከረ፤ ለይደር የሚተላለፍ ተግባር ሊሆን አይችልም። " ፖለቲካ ማለት ማድረግ የሚቻለውን ለማድረግ የሚያስችል ክህሎት ነው" () እስከተባለ ድረስ፤ መሆን የሚገባውን ሁሉ እየፈፀሙ ታግሎ ዓላማን ማሳካት ኃላፊነት፤ ለተተኪው ትውልድ የሚተላለፍ ሀኬት አይደለም ።

ጽንፈኛ ብሔረተኞች ፤ " ዛሬ ሁሉ በጃችን ሁሉ በደጃችን " ብለው ደንድነዋል ። የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው አካል፤ ያሻቸውን እንዲፈጽሙ አርንጓዴ መብራት ሰጥቷቸዋል ። ይኸ ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ ፤ አክራሪ ዘወገኞችን በአጥቂ ደርጃ ስያሰልፋቸው ፤ በገሃድ ኢትዮጵያዊነትን ያነገቡ

የፖለቲካ ኃይሎችን በመከላከል ደረጃ ላይ እንዲሆኑ አስገድዷቸዋል ። ለዚኽ ነው ዛሬ በሀገራችን፤ ፈንቃይ- ተፈናቃይ፤ አባራሪ- ተባራሪ- ዘራፊ ተዘራፊ፤ አሳዳጅ- ተሳዳጅ፤ ገዳይ ተገዳይ፤ ሁኔታ ጎልቶ ሊታይ የበቃው። ይኽ ሁሉ ችግር ፤ የብሔር/ብሔረሰብ ፖለቲካ ያመጣው ጣጣ ነው።

በኢትዮጵያዊነት የተደራጀው ኃይል፤ የልተነካ-ያልተዳሰሰ ዕምቅ አቅም ያለው መሆኑ ቢታውቅም፤ ወደ ተንቀሳቃሽና ተጨባጭ ኃይል ሊለውጠው አልቻለም ። ያ መሆን ከቻለ ደግሞ፤ ሳይንሳዊና ምክንያታዊ ብቻ ሳይሆን፤ የሠለጠነና የሰከነ ፖለቲካ ባኅል መስፈን ይጀምራል። ያ ከሆነ ደግሞ ፤ አዳዲስ ነፍጠኞች አድብ እንዲገዙ መገደዳቸው አይቀርም።

ዛሬ በየከልላቸው ካላሽን አንግበው ፤ ያዙን ሊቀቁን የሚሉ ዘመን -አመጣሽ ነፍጠኖች፤ " ከእኛ በላይ ጎራሽ፤ እህል አያበላሽ! " መባላቸው አይቀርምና፤ ሊጠነቀቁ ይገባል ። እነርሱ የጨበጡትን ሰደፍ፤ የሌላውም እጅ በሶ ስላልጨበጠ ፤ ካላሽን መጨበጥ አይሳነውም። ተያይዞ ከመጠፋፋት ይልቅ፤ ተዋውቆ፤ ተግባብቶና ተስማምቶ መኖሩ የማንንም ቤት አያፈርስም። የሁሉም ቤት ወና ሆኖ ከሚቀር፤ አደብ ገዝቶ ኢትዮጵያን የሁሉም ዜጋ ሀገር መኖሪያ እንድትሆን ማድረግ ለሁሉም ይበጃል !

የብሔር ብሄረሰብን መብት ማስጠበቅና የብሄር ፖለቲካ ማራመድ የተለያዩ ናቸው። የብሔር/ብሔረሰብን መብት እያጠበቁ ፖለቲካቸውን ኢትዮጵያዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያ፤ የሁሉም የጋራ ሀገር መሆኗን አምነው መቀበል የህልውናቸው መሠረት ነው ። ይኽ ደግሞ፤ ቅድመ-ሁኔታ እንጅ ፤ ለድርድርና ለክርክር የሚቀርብ አለመሆኑን መቀበል፤ ግዴታ ነው ። ይኽ መሠረታዊ ዕምነት፤ ቅድም- ቀዳድም፤ ዐልፋ- ዖሜጋ ፤ ቀዳማይ -ደሃራይ ነው። የሀገሪቱ ታሪክ መቅድም- መደምደሚያ ፤ መነሻ-መዳረሻ ፤ መኖሪያ መናሃሪያ ነው። ይኽንን ሃቅ መላው የዓለም ሀገሮች አምነው ተቀብለው፤ ተማምነው -ተስማተው ተቀብለው አምነው ተማምነው በአንድነት ይኖራሉ። ኢትዮጵያ ሀገራችን የዐለም ኅብረተስብ አባል እንደመሆኗ ፤ ከዐለም በተለየ ሁኔታ በቻውን ተገልላ ለመኖር አይሆንላትም። የዐለም ሀገሮች አመስራረትና ሂደት በግምት ወስጥ ባስገባ መልኩ ሊታይ ይገባል ከሚል አግባብነት ከተደረሰ፤ የአብዛኛዎች ሀገሮች አመስራረት፤ተወደደም ተጠላ፤ በኃይልና ከጦርነት ጋር በተየያዘ ሂደት እንደሆነ ማስረጃ ሊቀርብለት የሚችል ዕውነታ ነው።ለአብነት ያኽል የሚከተሉትን ሀገሮች እንደ ማጣቀሻ ማየት ይቻላል ፡-

**1ኛ.** በስፋቱ ከአንድ ውቅያኖስ ጫፍ እስከ ሌላኛው ውቅያኖስ ጫፍ ተንጣልሎ የሚገኘው የሩሲያ ሀገር የተመሰረተው በታላቁ ጴጥሮስ ንጉሠ ነገሥትና በታላቋ ንግስት ካትሪን የኃይል ርምጃና የዲፕሎማሲ ችሎታ ነበር።

**2ኛ.** በጥቃቅን ጉልተኞች ተከፋፍላ ስትገዛ የነበረችው ጀርመን የዛሬዋን ታለቅነት እንድታገኝ ያደረጋት፤ ቻንስለር ቢስማርክ ነበር። ቻንስለር ቢስማርክ፤ በዲፕሎማሲ ጥበብ፤ በታሪክ ስሙ የገነነ እንደነበር ብዙ ጻህፍት አረጋግጠዋል።

**3ኛ.** በትናንሽ መሳፍንት ተከፋለው የነበሩትን የኢጣሊያን ደካማ ግዛቶች፤ አንድ ጠንካራ ኢጣሊያ ሊያደርጋት የቻለው ፤ ጋሪባልዲ የተሰኘ ሀገር ወዳድ አንድ የጦር መሪ ነበር ። ኢጣሊያ ራሷን በማዋሃድ ፤ በዘመኑ ፤ያውሮፓ ጠንክራ ሀገር ከመሆን አልፋ-ተርፋ፤ ሀገራችንን ለመውረር በቅታለች። ያውም፤ በአርባ ዐመታት ውስጥ ሁለት ጊዜ !

የማስረጃዎቹን ብዛትና ርዝመት ዘርዝሮ መጨረስ የሚቻል አይመስለንም ። የዛሬዋ ዐለም ሀገሮች፤ አሁን የያዙትን ቅርፅ ከማግኘታቸው አስቀድሞ፤ ብዙ መለዋወጥ ማደረግ እንደነበረበባቸው መገንዘብ አስፈላጊ ነው ። የኢትዮያንም የዛሬውን መልከዐ- ምድር ፤ ከዚህ በተለየ መልኩ ማየት አይቻልም ። ይልቁንም፤ የዛሬዋን ኢትዮጵያና ዜጎቿን ነፃናትና አንድነት ጠብቆ በሠላም እንዲኖሩ ማድረግ ለድርድርም ሆነ ለጥያቄ የሚቀርብ ግን አይደለም ። ይኽ መሠረታዊ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፤ ሀገሪቱ፤ ሠላምና መረጋጋት አግኝታ ወደ ልማትና ዕድገት የምታመራበት አቅጣጭ ልትቀይስ የምትችለው ፤ ዲሞክራሲያዊ የሆነ ሥር ዓተ- መንግሥት ስትመሰርት ብቻ ነው ። ሠላም፤ አንድነት፤ ነፃነት፤ ልማትና ዕድገት ሁሉ የሚገኘው ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥር ዓት በማያሻማ ሁኔታ በሀገሪቱ ላይ መስፈን ሲችል ነው። ይኽ ሊሳካ የሚቸለው ደግሞ በሕዝብ ምርጫ የተሰየሙ፤ ባለ ራዕይ ዜጎች ሀገሪቱን ለማተዳደር ዕድል ሲያገኙ ይሆናል ።

ከታሪክ ዕስረኝነት ነፃ መውጣት፤ ሀገርንም ነፃ ለማውጣት ያስችላል። በታሪክ ጠባሳ ላይ እያተኮሩ፤ የትውልድን መፃኢ -ዕድል በዘውግ ፖለቲካ መመረዝ ፤ ለሃያ አንደኛው ዘመን አይፈይድም። ታሪክን በታሪክነቱ ብቻ ለአውንታዊም ሆነ ለአሉታዊ ግንዛቤ እያስቀመጡ መኖር ግን ለሁሉም ዜጋ ይበጃል ። ፤ ሀገር ተረካቢውን ትውልድ፤ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የሚኖር ዜጋ እንደሆነ በማመን፤ በሠላም ተስማምቶ አንድ ላይ እንዲኖር ማድረግ ያሁኑ ትውልድ ኃላፊነ አለበት። ይኽንን ማድረግ ከቻለ ፤ ከታሪክ ተወቃሽነት ነፃ ይወጣል ። እራሱን ነፃ ያወጣ ትውልድ፤ ሌላውን ነፃ የመውጣት፤ የኀሊና ግዳጅ

ሊኖረው ይችላል። ግዳጅን መወጣት ደግሞ፤ የዜጋ ፖለቲካ አራማጆች መርኅ ሊሆን ይግባል ። በዚህ ሀቅ መስማማት ከተቻለ፤ ዜጎችና ዘውገኞች ከቁጭትና ከዕልኅ ነፃ ሆነው፤ ለነገዋ ኢትዮጵያና ለዜጎቿ አብሮ የመኖር መልካም ዕድል ማመቻቸት ይችላሉ። አዲስቷን ኢትዮጵያ ፤ ለመግንባት ሁሉም ዜጎች የሚተባበሩበትን ሀገራዊ መድርክ ማመቻቸት፤ በአደራም ሆነ በቀላጤ የሚሆን ተግባር አይደለም። ሁሉም ዜጋ ሊሳተፍበት የግድ ይላል ። ሀገር ለመገንባት የሁሉንም ጥረትና መሥዋዕት ይጠይቃል። ሀገር መገንባት ከባድ ዋጋን የሚያስከፍል መሆኑን ካልተገነዘቡ፤ ማኸል መንገድ ሲደርሱ ተስፋ መቁረጥ እንዳይመጣ ከመጀመሪያው ሊታሰብበት የሚገባ ይመስለናል ። የሀገራችን ፖለቲካ ትግል ፤ የጥሎ ማለፍ ዕግር ኳስ ጨዋታ እንዳልሆነ ፤ መራራው የትግል ታሪካችን በሚገባ አስተምሮናል። ከዚህ ሀቅ በመነሳት፤ ለዜግነት ፖለቲካ ታጋዮች የምናከፍላቸው ኃስብ ቢኖረን፤ " **መለበሚያ አታድርገኝ፤ መለበሚያ ግን አትንሳኝ** " የሚለውን ብሂል እንዲያስትውሉት ነው።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ጨቋኝ አገዛዞችን ተባብሮ ማስወገድ በተደጋጋሚ አስመስክሯል። እነርሱን እየስወገድ ግን መተኪያቸውን ለመተካት ግን አልሆነለትም ።

**ሀ.** የዐፄውን ሥርዓት ጥሎ እርሱን በሚተካው ላይ ባለምስማማቱ ፤ የደርግ አምባገነን፤ ዡሮው እየሰማ፤ ዐይኑ እየየ መጣባት።

**ለ.** ደርግን ለማስወገድ አይከፍሉ መሥዋዕት ቢከፍልም ፤ ደርግ ተባርሮ ፤ መተኪያውን ሳያሰናድ በመቅረቱ ፤ የዘረኛ ሥርዓት በወያኔ ሲተካ አሁንም እንደገና ወደ ሦስተኛ ዙር የትግል ጉዞውን ቀጠለ።

**ሐ.** የወያኔው ሸንኮፍ በመራራ ትግል ቢሽመደመድም፤ አሁንም ይኸን ዘረኛ ሥር ዓት ለመተካት ገና ብልኃት አላገኘም።

ላለፉት አምሳ ዐመታት ከተፈራረቁብን ስኅተቶች ፤ አሁንም መማር አልተቻልም ። እንደ ስኅተታችን ተደጋጋሚነት ዛሬም፤ ያው ብልሃቱን ለማግኘት ሳማይ -ምድሩ ተድፍቶብናል። የምንይዘው -የምንጥለው ጥፍቶብናል። የችግራችንን ከብደት ስፋትና ጥልቀት ፤ በድርጅቶች ብዛት ይወገድልናል ብለን በመመኘት ፤ ዛሬ ብዛታቸው ከአንድ መቶ በላይ የሚቆጠሩ ፓርቲዎች ፈጥረን ቁጭ ብለናል ። አብዛኛዎቹ የዘውግ ድርጅቶች ናቸው ። በታዛቢዎቻችን ዘንድ፤ " **የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ።**" የሚል ሽሙጥ ይሰነዘርብናል ። እንደ ምድረ-በዳው ነጋዴ፤ ለውደቅ የምትንገዳገደዋን ግመል፤ አርዶ ለመብላት ካራውን እንዳበዛ ሁሉ፤ ሀገራችንም የዚያ ዕድል እንዳይገጥማት፤ ልናስብበት ይገባናል !

ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኖራለች !